# ልሳቅ ወይስ ላልቅስ



*

ቃሊቴ ይባላል መኖሪያ ቤታቸው፤

እኔህ ወገኖቸ፣ እህቶች፣ ልጆቸ

ምን ቤት ቢጠፋ ነው

በዚያ መታጨቃቸው?

እባክህ አስረዳኝ ክርስቴያን ነኝ ያልኸው፤

ስምህ ደስተኛ የአባትህም ስያሜው

ለማርያም ክብር ነው።

እስኪ ልጠይቅህ ቃሊቲ ለመሄድ

አቅጣጫው በየት ነው?

ይህነን ሰማሁኝ

እህት ወገኖቸን ከዚያ እንዳጎርሃቸው።

ደግሜ ልጠይቅህ ሰከን ባለ አንደበት

ያንተ እሴቶ ልጆች

የት ቦታ ነው ያሉት?

እየጣሩ ይሆን

እውቀት ለመገንባት፤

በድሚ የገፋህ ለት

አንተን ለመትካት?

የድሆች ልጆች ግን

ታጭቀው ነው ያሉ በቃሊቲ እስር ቤት።

**ልሳቅ ወይስ ላልቅስ** ለሚመጣው ይዘት

ወዮ አንተን አያርገኝ ሕዝቡ ያመጸ ለት።

እባክህ አዳምጠኝ አንት የጴንጤው ጓዴ፤

እሁድ ስትጸልይ ምኑን ጠቅሰህ ይሆን

የመለስን ወንጌል ወይስ አደገደግህ የሊነን ጎራዴ።

እባክህ አስረዳኝ

**ልሳቅ ወይስ ላልቅስ፤**

ቅሊቲን ሳስታውስ።

ወንጌልን አዛብተው አሉህ ኃይለማርያም፤

አስተውል አንተዬ

ኃይል የእግዚአብሔር እንጅ የጠብመንጃ አይደለም።

የነፃ አውጭው ጓዴ፣ ሱማሌ አገር ሄዶ

የኢትዮጵያን ይዘት ሰወች ቢጠይቁት፤

ሱዳን አገር ሄዶ ሰለ ኢትዮጵያ እስር ቤት

ሰወች ቢጠይቁት፤

እንዲህ ሴል መለሰ፣ ላለፈው አትጠይቁኝ፤

**በጎሣ በክልል** ታሪክ ፈጣሪ ነኝ።

የደም እንባ አታልቅሱ የኢትዮጵያ እናቶች

ለሴት ልጆቻችሁ፤

በዚያ በቃሊቲ ስለታቆሩባችሁ።

የኔ እንኳን ጥያቄ አሁንም እንዲህ ነው

ስለተነገረኝ ቃሊቴ ይባላል መኖሪያ ቤታቸው፤

እኔህ ወገኖቸ፣ እህቶች፣ ልጆቸ

ምን ቤት ቢጠፉ ነው በዚያ መታጨቃቸው?

አዳምጠኝ ወገኔ ይህን እሮሮየን

**ልሳቅ ወይስ ላልቅስ፤**

ቃሊቲን ሳስታውስ?

ደግሞም እሰጋለሁ ለገመቹም ሆነ ለመሐመድ ከድር፤

እውነቱ በመውጣት እሱም ይታጎራል

ቅን ፈራጅ ሲመጣ በእትዮጵያ ምድር።

*photo from http://ecadforum.com/Amharic/archives/16227/

© ለምለም ፀጋው፣ March 9, 2016